# ተጽፏል…

በሚስዮናዊ ኢ. ፍራንክ የተዘጋጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንታኔ

# ተጽፏል...

## መቅድም

የሰማይ አምላክ - የዩኒቨርስ ፈጣሪ - በምድር ላይ ከሰው ልጆች ጋር ያለውን ግንኙነት መስርቷል። የዚህ ቡክሌት ደራሲ እንደመሆኔ መጠን፣ አንባቢውን ከብቸኛ፣ እውነተኛ እና ህያው የሆነዉን አንድ እግዚአብሔር እና ለሰው ልጆች ካለው እቅድ ጋር ለማስተዋወቅ እፈልጋለሁ። በዚህ ትንታኔ ውስጥ ጥቂት ነገሮችን ብቻ ነው የምንመለከተው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ በአንባቢዎች ልብ ውስጥ በጥልቀት ለመፈለግ ፍላጎትን እንደሚፈጥር ተስፋ እናደርጋለን።

እኛ የአንድን የተወሰነ ቤተ እምነት አመለካከት አንወክልም፣ ይልቁንም እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉ ለራሱ ይናገር ዘንድ እንፈቅዳለን። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ምርጫና ውሳኔ ከአብርሐም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ እንዲሁም በሌሎች ነቢያት አማካኝነት እንደሚያውቅ፣ እኛም ጌታ ለተለየ ዓላማ በመረጣቸው ሐዋርያትና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በነበሩ ሰዎች አማካኝነት እንዲሁ እናደርጋለን።

ለእርሱ ባለን ጥልቅ አድናቆት፣ በእኛ ዘመን ከእግዚአብሔር የተላከ የአንድ ሰው አገልግሎትን እንጠቅሳለን። የተመረጠውን ዕቃ ከፍ ለማድረግ በፍጹም አንፈልግም፣ ክብርን ግን ለሰማያት አምላክ ብቻ እንሰጣለን። ጌታ አሁን እያደረገ ያለውን ማንኛውንም ነገር ማለፍ አንችልም። እባክዎን አሁንም በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ውስጥ እንዳለን ያስታውሱ። ጌታ አልሞተም - ተነስቷል እናም እርሱ ቃል እንደገባልን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእኛ ጋር ነው።

ይህ ብሮሹር በዋናው ቋንቋ ታትሞ በመቶዎች በሚቆጠሩ የአለም ሀገሮች ውስጥ ይነበባል። ምናልባትም በተለያዩ ሃይማኖቶች እና እምነቶች እጅ ሊወድቅ ይችላል። ማንኛውም አስተዋይ ሰው በሰው የተጀመረ ማንኛውም ነገር ሊሳሳት የሚችልና ለስህተት የተጋለጠ መሆኑን ያውቃል። ስለዚህ ወደማይሳሳተው ብቸኛ ምንጭ መዞር አለብን።

እያንዳንዱ አንባቢ ከዚህ አጭር ትንታኔ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ይጠቅምና ከጌታ ጋር ያለውን የግል ግንኙነት ያገኝ ዘንድ ጸሎቴ ነው።

**ደራሲው**

# ተጽፏል

በእጃችን ልንይዘው የምንችለው ታላቁ ሀብት የተጻፈዉን የእግዚአብሔር ቃል ነው፣ ምክንያቱም ሰማይና ምድር ያልፋሉ፣ የእግዚአብሔር ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል። ለሰው ልጆች ያለው እቅዱም በውስጡ ተገልጧል። የተነገረው ቃል ወደ ነቢያት መጣና ተጻፈ። በኋላም ሐዋርያት የተመረጡ ምስክሮች ነበሩ። ስለዚህ ሁለቱም ብሉይ እና አዲስ ኪዳን አሉን። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሁሉንም ጥላዎች፣ ዓይነቶች እና ተስፋዎች እናገኛለን፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ደግሞ እያንዳንዱ ቅዱሳት መጻህፍ ቃል በቃል እንዴት እንደተፈጸመ የሚገልጽ እጅግ አስደናቂ የሆነ መዝገብ አለን። ይህ ደግሞ አሳማኝ የሆነው ክፍል ነው።

አዲስ ኪዳን ትንቢቶች በተግባር ሲፈጸሙ መጀመሩ ትኩረትን የሚስብ ነዉ። ዮሐንስ ቃል የተገባዉ ነቢይ ሲሆን፣ አዳኛችን ደግሞ ቃል የተገባዉ ቤዛ ነው። እውነተኛ እምነት በእግዚአብሔር በተሰጠው የተሰፋ ቃል ላይ የተመሰረተ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ፣ ህይወቱ፣ አገልግሎቱ፣ መከራው፣ ሞቱ፣ ቀብሩ፣ ትንሣኤው እና ዕርገቱ፡ ሁሉም ነገር በነቢያት እንደተተነበየው በትክክል ተፈጽሟል። በእርግጥም፣ እግዚአብሔር ታሪክን ከመቶዎች እና ከሺህዎች ዓመታት በፊት እንዲጻፍ አድርጓል። ይህ አስደናቂ እና ግርማ ሞገስ ያለው ነው። የታሪክ ጸሐፊዎች ክስተቶች ከተፈጸሙ በኋላ በመጻፍ ይጠመዳሉ። እግዚአብሔር ከመጀመሪያው መጨረሻውን አይቷል፣ ስለዚህም ሁሉንም ነገር አስቀድሞ እንዲጻፍ ማድረግ ችሏል።

በጌታችንና መድኃኒታችን የመጀመሪያ ምጽአት ጊዜ ከመቶ በላይ የሚሆኑ ትንቢቶች ተፈጽመዋል። ከዘፍ.3፡15 የሴቲቱ ዘር የእባቡን ራስ ለመቀጥቀጥ ይመጣል ከተባለው ትንቢት እስከ ሚል.3፡1 ጌታ ወደ ቤተ መቅደሱ ይመጣል እስከሚለው ትንቢት ተፈጽሟል። **"እንደ ተጻፈው" ወይም "ቅዱስ ጽሑፉ እንደሚለው" ወይም "በነቢያት የተነገረው ይፈጸም ዘንድ"** የሚሉትን ቃላት ባገኙበት ቦታ ሁሉ ሆን ብሎ ምልክት በማድረግ አዲስ ኪዳንን በጸሎት ማንበብ ለሁሉም ሰው ይመከራል። በሉቃስ 24 ላይ ጌታ ለተወሰኑ ደቀ መዛሙርቱ ከሙሴ፣ ከመዝሙራት እና ከነቢያት በመነሳት ተናግሮ፣ ሁሉም ነገር እንደተፈጸመ አረጋግጧል። ኢየሱስ ክርስቶስ ያዉ ስለሆነ፣ አሁን እየተፈጸሙ ያሉትን ቅዱሳት መጻሕፍት ይጠቁመናል። እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግ ማወቅ ካለብን፣ መጀመሪያ የሰጠውን ተስፋ ማወቅ አለብን።

የሙሴ ጩኸት የእኛም ነው፣ "እንግዲህ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ፣ እባክህ መንገድህን አሳየኝ..." (ዘጸ.33፡13)። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በቃሉ መሠረት ያደርጋል እናም "ሀሳቤ እንደ ሀሳባችሁ አይደለም፣ መንገዳችሁም እንደ መንገዴ አይደለምና ይላል ጌታ። ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፣ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ፣ ሀሳቤም ከሀሳባችሁ ከፍ ያለ ነውና" (ኢሳ.55፡8-9) ። በእርግጥም ከእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ያገኘ ማንኛውም ሰው ከሕዝቡ ጋር ያለውን መንገዱን ይገነዘባል እናም በዚህ ጊዜ እያደረገ ባለው ነገር ሁሉ ይካፈላል። ምን እንደምንጠብቅ እርግጠኛ ለመሆን ከመቼውም ጊዜ በላይ ቅዱሳት መጻሕፍትን መመርመር አለብን።

አብዛኛው በቤተክርስቲያን ያሉ መመምህራን "እንደተጻፈው ነው" በማለት ቅዱሳት መጻሕፍትን ስለሚጠቅሱ እና በተመሳሳይ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል በስህተት

ስለሚተረጉሙ፤በስህተት ስለሚጠቀሙ እና ከአለ ስፍራዉ ስለሚያስቀምጡ ትልቅ ችግር ይፈጠራል። ኢየሱስ በዘመኑ የነበሩትን የሃይማኖት መምህራን በዚህ ሁኔታ ውስጥ አገኛቸው። በሰዎች ትእዛዝ ትምህርትን በማስተማር የእውነተኛውን የአምላክ ቃል ለሰዎች ከንቱ አድርገው ነበር (ማር.7፡13)። ከጥንት ጀምሮ የአለዉ ጠላት የእግዚአብሔር መኖርን (ያዕ.2፡9) ወይም ቃሉን (ሉቃስ 4፡1-13) አይክድም። በቀላሉ የራሱን ትርጓሜዎችና የጥያቄ ምልክቶችን ከኋላው ያስቀምጣል። አንድ ሰው "ተብሎ ተጽፏል፣ ተብሎ ተጽፏል" ብሎ ደጋግሞ መናገር እና ራሱን ከላይ እስከ ታች በመጻህፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስዋብ ይችላል፣ ነገር ግን መለኮታዊ መገለጥ ላይኖረዉ እና ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ሊሆን ይችላል። በመገለጥ እና በመተርጎም መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። አንዱ ከእግዚአብሔር ይመጣል፣ ሌላው ደግሞ ከሰይጣን ይመጣል - አንዱ ሕይወትን ያመጣል፣ ሌላው ደግሞ ሞትን ያመጣል። አዳም እና ሔዋን በእግዚአብሔር ቃል ሲያምኑና ሲታዘዙ የዘላለም ሕይወት ነበራቸው፣ የጥንቱን እባብ ማብራሪያ ሲያዳምጡ ግን ሞት መታቸው (ዘፍ.3)። ብዙዎች የሕይወትን ዛፍ ትተው የእውቀትን ዛፍ ተከትለዋል እና በእራሳቸዉ ዉስጥ አዋቂ ሁነዋል-እግዚአብሔርን የመምሰል መልክ አላቸዉ ኃይሉን ግን ክደዋል (2ጢሞ.3፡5)።

ክርስቶስ በአርባ ቀናት ቆይታው በሰይጣን ሲፈተን ጠላት "ተብሎ ተጽፏል..." ለማለት መደፈሩ ትኩረት የሚስብ ነው። ከኤደን ገነት ጀምሮ የእግዚአብሔርን ቃል በተሳሳተ መንገድ ሲተረጉም እንደነበር ግልጽ ነው። ያ ደግሞ አደገኛው ክፍል ነው። እስከ መጨረሻው ድረስ ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በግል እንዲተረጎሙ ሰዎችን በመጠቀም ያታልላል፤ማንም ለገዛ እራሱ ሊተረጉም ያልተፈቀደዉን (2ጴጥ.1፡20)። ሁሉም የሐሰት ነቢያት (ማቴ.24፡24) እና ሁሉም የሐሰት ሐዋርያት (2ቆሮ.11፡13) ራሳቸውን በክርስቶስ የተላኩ እንደሆኑ አድርገው ያቀርባሉ።ሰይጣን ራሱን የብርሃን መልአክ አድርጎ ያሳያል። "ስለዚህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅ አገልጋዮች መስለው ራሳቸዉን ቢለወጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜያቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል።" (2ቆሮ.11፡14-15)

**የእግዚአብሔር የተስፋ ቃልን ማጣጣም(መለማመድ) ይገባል፤ማብራራት ሳይሆን።**

**የእግዚአብሔር ትንቢታዊ ቃል ሲፈጸም ሊታይ ይገባል።**

ጌታችን ቅዱሳት መጻሕፍትን የመጠቀም መብት ነበረው፣ በዚህም ሰይጣንን አሸነፈዉ። ለዛሬ የተሰጠው የተስፋ ቃል በአማኞች በኩል ከተገለጠ፣ እነርሱም እርሱን የመጥቀስ መብት አላቸው። እውነተኛው ቃል የሚሰበክበትን ቦታ እና ክርስቶስ ራሱ በስሙ እንዲናገሩ የመረጣቸውን ሰዎች እንዴት ማወቅ ይቻላል? የሚለው ጥያቄ ይነሳል። ኢየሱስ ስለላካቸው ሰዎች "እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል" (ማቴ.10፡40) ብሏል። እርሱም ደግሞ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ማናቸዉን የምልከዉን የሚቀበል እኔን ይቀበላል..." (ዮሐ.13፡20) ብሏል። በመጨረሻም ለመንፈሳዊ አገልግሎት ስለመረጣቸው ሰዎች "አብ እንደላከኝ እኔም እልካችኋለሁ" (ዮሐ.20፡21) ብሏል።

በእግዚአብሔር የተጠራ እውነተኛ ሰው ሁሉ ጳውሎስ የጻፈውን መናገር መቻል አለበት፣ “ወንድሞች ሆይ፣ በእኔ የተሰበከ ወንጌል እንደ ሰው እንዳይደለ አሳውቃችኋለሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል እንጅ እኔ ከሰው አልተቀበልሁትም፤ አልተማርሁትምም።” (ገላ.1፡11-12)።በተመሳሳይ መልኩ የሐዋርያው ጴጥሮስ ቃልም አስፈላጊ ነው፣ “…በወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃልም ይህ ነው” (1ጴጥ.1፡25)። ሐዋርያው ዮሐንስ በጣም ጠንካራ የሆነውን መግለጫ አቅርቧል፣ “እኛ ከእግዚአብሔር ነን፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል። ከእግዚአብሔር ያልሆነ አይሰማንም። የእውነትን መንፈስ እና የስህተትን መንፈስ በዚህ እናውቃለን” (1ዮሐ.4፡6)።

ጌታችን ኢየሱስ “እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና…” (ዮሐ.3፡34) ብሏል።በዮሐ.8፡43 ላይ ደግሞ “ንግግሬን የማትረዱት ስለምንድን ነው? ቃሌን ልትሰሙ ስለማትችሉ ነዉ” ብሎ ጠየቀ። በቁ.47 ላይ ደግሞ “ከእግዚአብሔር የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል፤ እናንተ ከእግዚአብሔር ስላልሆናችሁ፣ ስለዚህ አትሰሙም” ብሏል። በእነዚህ የጌታችን ቃላት መሠረት፣ ሁሉም ሰው ያለ ምንም ውስጣዊ ተቃውሞና ክርክር እያንዳንዱን የእግዚአብሔርን ቃል ይቀበል እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ራሱን የመፈተሽ ዕድል አለው። ብዙውን ጊዜ ሰባኪው የመጽሐፍ ቅዱስን ጽሑፍ ያነባል እና በራሱ ሐሳብ ያቀርባል፣ ይህም ከእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ወሰን ውጭ ነው። የመጨረሻው የማጣራት ጊዜ አሁን ነው። ሁሉንም ነገር መፈተሽ አለብን።

የምናምነውና የምናደርገው ነገር ሁሉ በመጀመሪያ የቃል ፈተናዉን ማለፍ አለበት። ጳውሎስ ባገኘው መገለጥ ምክንያት ትምህርቱን ከመጀመሪያው ከተማረው ከዋናው ቃል ጋር ለማነጻጸር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። “የምሮጠው ወይም የሮጥሁት በከንቱ እንዳይሆን” በማለት በአሕዛብ መካከል ያስተምር ስለነበረው ትንታኔ ሰጥቷል (ገላ.2፡1-3)። የተሳካ አገልግሎት ስብከቱ እውነት መሆኑን አያረጋግጥም። በእግዚአብሔር ፊት አጋንንትን ማውጣት፣ ተአምራት እና ትንቢት መናገርም እንኳ በቂ አይደለም (ማቴ.7፡21)። ኢየሱስ በመጨረሻዎቹ ቀናት ብዙ የተቀቡ ሰዎች ስለሚነሱ አስጠንቅቆናል፣ “የሐሰት ክርስቶሶችና የሐሰት ነቢያት ይነሣሉና፣ ቢቻልስ የተመረጡትን እንኳ እስከማሳት ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ።” (ማቴ.24፡24)። ጳውሎስ እንዳደረገው፣ ስብከታችንንና ተግባራችንን ከመጀመሪያው “የሐዋርያት ትምህርት” (ሐዋ.2፡42) ጋር ማነጻጸር በጣም አስፈላጊ ነው።

ከቃሉ መለየታቸዉን በማወቅ ጌታችን ዛሬም “ትምህርት አድርገው የሰዎችን ስርአት ስለሚያስተምሩ በከንቱ ያመልኩኛል” (ማር.7፡7) ይላል። እግዚአብሔር በቃሉ መሠረት ያልተደረገውን ማንኛውንም ነገር አይቀበልም። “እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል” (ዮሐ.4፡24)። የእውነት **ቃል** እና **የእውነት መንፈስ** ሁልጊዜም አብረው ይሆናሉ። የሚሰብኩትና የሚሰሙት ነገሮችን ከራሳቸው አመለካከት አንጻር ሊፈርዱ አይገባም፣ ነገር ግን በማይሳሳተው ቃል ላይ ቆመው ነገሮችን በእግዚአብሔር መንገድ መመልከት አለባቸው።

## በመንፈስ አንድ መሆን

አንድ የመሆን ናፍቆት ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ያህል የቆየ ነው:: ከመጀመሪያው ጀምሮ ሰው ይህን አንድነት ለማሳካት ሞክሯል:: ነገር ግን በእግዚአብሔር በተወሰነዉ መንገድ ካልተገኘ፣ በእርሱ ፊት ሊቆም አይችልም:: የእግዚአብሔር ሕዝብ አንድ የሚሆንበት ጊዜ በእርግጥ ደርሷል:: አንድ - ግን በምን መንገድ? በተጻፈዉ የእግዚአብሔር ቃል መመለስ ያለባቸው አሳሳቢ ጥያቄዎች አሉ:: ሰዎች ስለ እንደዚህ ዓይነት አስፈላጊ ጉዳይ የሚናገሩበት ጊዜ ማብቃት አለበት:: ይህ የእግዚአብሔር ሕዝብ ግልጽ የሆነውን እውነት የሚሰማበት ጊዜ ነው:: የሰዓቱ በጣም አስፈላጊው ጭብጥ ስለ አንድነት፣ ሰላም እና ደህንነት ጩኸት ሆኗል:: የመንግሥት መሪዎችና ተደማጭነት ያላቸው የሃይማኖት መሪዎች በዚህ አንድ ታላቅ ጥረት ውስጥ ይተባበራሉ:: ወደ ተለያዩ የሙሉ ወንጌል እንቅስቃሴዎች ስንመለከት፣ ተመሳሳይ ጩኸት እንሰማለን፣ እንዲያውም ይበልጥ ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጽንዖት የቀረበ ነው:: ሁሉም የዮሐ.17፡21ን ጥቅስ "...ሁሉ አንድ ይሆኑ ዘንድ" ይጠቀማሉ:: ጌታ ስለነማን ነበር የሚይናገረዉ? ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ ለማን ነበር የጸለየው? ስለ አንድነትና አንድ ስለመሆን የሚናገሩት የተለያዩ ዓላማዎችና ግቦች አሏቸው::

በዘፍ.11 ላይ የነበሩ ሰዎች አንድ እንደነበሩ እናነባለን:: አንድ ቋንቋ እና አንድ የጋራ ግብ ነበራቸው:: ለመገንባት በሞከሩት ግንብ አማካኝነት ወደ ሰማይ መድረስ ነበር፣ እናም በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እንደተገለጸው ለራሳቸው ስም ማውጣት ፈልገው ነበር:: ይህ የዛሬው ምስል ሊሆን ይችላል? ልንማረው የሚገባን በጣም አስፈላጊ ትምህርት **የእግዚአብሔር ነገሮች በሰው መንገድ ሊከናወኑ አይችሉም**::

አንድ የመሆንን የተለያዩ መንገዶች ለማሳየት ጥቂት ምሳሌዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት ሊወሰዱ ይችላሉ:: በ1ነገሥት 22 እና በ2ዜና መዋዕል 18 ላይ አንድ የሆኑ፣ ተመሳሳይ ነገር የሚናገሩ 400 ነቢያት እናገኛለን:: የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ የይሁዳን ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ከእርሱ ጋር ወደ ጦርነት እንዲሄድ ጠየቀው:: ንጉሡ ክብር ተሰማው፣ ተስማማ እና "እኔ እንዳንተ ነኝ፣ ሕዝቤም እንደ ሕዝብህ ነው፣ ፈረሶቼም እንደ ፈረሶችህ ናቸው" አለ::

እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው የነበረው ኢዮሣፍጥ ከጌታ መስማት ስለፈለገ ንጉሥ አክዓብን "እባክህ ዛሬ የእግዚአብሔርን ቃል እንጠይቅ" አለው:: የ400ዎቹን ትንቢት ተጠራጠረ:: በታላቅ ቅብዓት ሥር ሆነው "ወደ ራምዖት ገላት ውጣ፣ ጽናም፤ እግዚአብሔርም በንጉሥ እጅ አሳልፎ ይሰጣታል::" ኢዮሣፍጥ በዚያ በአንድነት በተነገረው ትንቢት ዕረፍት አላገኘም እና "ከዚህ ሌላ፣ እኛ የምንጠይቀው የእግዚአብሔር ነቢይ የለምን?" አለ::

ትዕይንቱን አስቡት፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ነቢያት በአንድነት ተስማምተዋል፣ ነገር ግን ንጉሥ **አንድ ሰው**፣ የጌታ እውነተኛ ቃል ያለው አንድ ሰው ብቻ ይጠይቃል (1ነገሥት 17፡24)! ይኸ ዛሬ ያስፈልገናል:: አሁን ብዙዎች በተባለው "ወንድማዊ መንፈስ" ውስጥ በአንድነት ናቸው፤ ፕሮቴስታንቶች፣ ካቶሊኮች እና የተለያዩ ሃይማኖቶች አንድ ላይ እየመጡ ነው:: ሆኖም፣ ጌታ በንጹሕ ቃሉ የተናገረውን የማወቅ መብት አለን::

አክዓብ "እኔ ግን እጠላዋለሁ" ያለው ሚክያስ በግልጽ እንደምናየዉ በዘመኑ ከነበረው የተደራጀ ማህበር ዉስጥ አልነበረም:: እርሱ ከቤተ እምነት ውጭ ነበር፣ ነገር ግን

በእውነተኛው መንፈስ ቅብዓት ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነበር:: ራሱን የሾመው ዋና ነቢይ ሲድቅያስ ከብረት ቀንዶች ሠራ እና "ጌታ እንዲህ ይላል…" አለ፣ የተቀሩትም በአንድነት ከእርሱ ጋር ተስማሙ::  እንዴት ያለ ታላቅ ስብሰባ ነው! ግን ሁሉም በሐሰተኛ መንፈስ ሥር ነበሩ፣ ሁሉም ተታለው፣ "ጌታ እንዲህ ይላል…" በማለት ተመሳሳይ ነገር ይተነብዩ ነበር!

ሚክያስን ለመጥራት የተላከው መልእክተኛ ከሌሎቹ ጋር እንዲቀላቀል እና እነርሱ የሚሉትን እንዲናገር ነገረው:: የእግዚአብሔር ሰውም "እግዚአብሔር ሕያው እንደሆነ፣ እግዚአብሔር የነገረኝን እርሱን እናገራለሁ" ብሎ መለሰ::  በእርግጥም ነቢያቱ እውነት ተናገሩ:: እሱ ራዕይ አይቶ ነበር (2ዜና.18፡18-22) እናም በሰማይ የተደረገውን ውይይት ሰምቷል:: ራዕዩ ስለ አክዓብ ፍርድ ከነቢዩ ኤልያስ ከተነገረው የጌታ ቃል ጋር ሙሉ በሙሉ ይስማማ ነበር (1ነገሥት 21፡19፤ 22፡38)::

ሚክያስ ለንጉሡ በጣም እርግጠኛ ስለነበር ከጦርነት ከተመለሰ በኋላ ሊገድለው ለፈለገው ንጉሥ "በደህና ብትመለስ ጌታ በእኔ የተናገረ አይደለም " አለ:: "እናንተ ሕዝብ ሁሉ ስሙኝ" በማለት አጽንዖት ሰጥቶ ተናገረ :: **ማነኛውም እውነተኛ ነቢይ በማነኛውም ጊዜ በጌታ ስም ከተናገሩ ነቢያት ሁሉ ጋር ሙሉ በሙሉ መስማማት አለበት**:: ይህም ለሐዋርያ፣ ለአስተማሪ፣ ለወንጌላዊ - በክርስቶስ አካል ውስጥ ላለ ማንኛውም አገልግሎትም ይሠራል::

## ሁኔታው

በብዓለ ሃምሳ ቀን፣ 120ዎቹ በአንድ ልብ ነበሩ:: እነርሱም ከስአቱ ቃል ጋር "አንድ ሆነዉ" ነበር:: አሁን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ለመሆን፣ ለዚህ ጊዜ ከተሰጠዉ ቃሉ ጋር አንድ መሆን አለብን:: ኢየሱስ "አንተ፣ አባት ሆይ፣ በእኔ እንዳለህ፣ እኔም በአንተ እንዳለሁ ሁሉ፣ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ" ብሏል:: ወልድ የአብ የግል መገለጥ ነበር - ተመሳሳይ ማንነት፣ ተመሳሳይ መንፈስ፣ ተመሳሳይ ሕይወት::

ወልድ በመንፈስ ቅዱስ ተወልዷል፣ ይህም ለድንግል ማርያም በተሰጠው ተስፋ ውስጥ ተመዝግቦ እናገኛለን፣ በሉቃስ 1፡35 "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኃይል ይጋርድሻል" በማቴ.1፡20 ላይም ተመሳሳይ ነገር ተረጋግጧል:: መንፈስ ቅዱስ ተስፋውን ተቀብላ ባመነችው ማርያም ላይ ወረደ::  በዚህም ቃል ሥጋ ሆነ እና በእኛ መካከል አደረ:: የአብና የወልድ አንድነት ስምምነት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን፣ በባህሪ(essence) አንድነት ላይ የተመሰረተ ነው:: ይህም ከሁሉም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ጋር ተመሳሳይ ነው:: እነርሱም በተመሳሳይ ቃል፣ በተመሳሳይ መንፈስ እንደገና ተወልደዋል፣ ስለዚህም ተመሳሳይ የሆነ መለኮታዊ ባህሪ ተካፋዮች ናቸው (2ጴጥ.1፡4)::

የእየሱስ ክርስቶስ ተመሳሳይ ባህርይና የኢየሱስ ክርስቶስ አይነት ሕይወት ያላቸው እነርሱ ብቻ በመንፈስ አንድ ሊሆኑ ይችላሉ:: ያዕቆብ "ለፍጥረቱ የበኩር ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን" (1፡18) ብሎ ጽፏል:: ኢየሱስ አንድያ ልጅ ነበር፣ እኛም የእርሱ ዓይነት፣ የተወለዱ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች መሆን አለብን:: በዚህ ረገድ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት "ከብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ" (ሮሜ.8፡29)

ብለው ስለ እርሱ ይናገራሉ። በእግዚአብሔር የመራባት ሕግ መሠረት፣ ከዘፍጥረት ጀምሮ እያንዳንዱ ዘር እንደ የወገኑ ያፈራል። ከእግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር ብቻ ሊወጣ ይችላል፤ ከእግዚአብሔር ልጅ፣ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ብቻ ሊወጡ ይችላሉ። ጴጥሮስም ተመሳሳይ እውነትን "ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሳቱ ለሕያዉ ተስፋና ለማይጠፋ፤ እድፈትም ለሌለበት፤ለማይልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤ በብዙ ምሕረቱ ከሙታን በትንሣኤው ወደ ሕያው ተስፋ እንደገና ወለደን..." በማለት አጽንዖት ሰጥቷል (1ጴጥ.1፡3)።

ኢየሱስ "እኔን ያየ አብን አይቷል" (ዮሐ.14፡9) ማለት ችሏል። ባልና ሚስትም አንድ እንደሆኑ ተነግሯል። ነገር ግን ማንም ሰው "እኔን አይተህ ከሆነ ሚስቴንም አይተሃል" ማለት አይችልም። ኢየሱስ የሚናገረው መንፈሳዊ አንድነት እርስ በርስ መስማማት ወይም መጣመር ሳይሆን፣ የተለየ መገለጥ ቢሆንም፣ ተመሳሳይ ማንነት መሆን ማለት ነው። ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን መቀላቀል አይችልም - አንድ ሰው መወለድ፣ መጠመቅ እና በውስጡ መታተም አለበት።

ወደ ዮሐ.17፡21 ላይ ወደተደረገው መግለጫ እንመለስ፡ "አንተ፣ አባት ሆይ፣ በእኔ እንዳለህ፣ እኔም በአንተ እንዳለሁ ሁሉ፣ ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ።" ይህ የመለኮታዊ አንድነት ምስጢር ነው፡ አምላክ በክርስቶስ - ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያኑ።

ኢየሱስ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እየጸለየ ነው እንጂ እየሰበከ አይደለም። የተናገረው ነገር መፈጸሙን በመጠበቅ በጸሎት ሊታሰብበት የሚገባ ነው። በዮሐ.17 መሠረት የዚህ አንድነት አንዳንድ መመዘኛዎች፡

"...ለሰጠኸው ሁሉ የዘላለም ሕይወትን ይሰጣቸዉ ዘንድ"

"ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸዉ"

"አንተ የሰጠኸኝን ቃል እኔ ሰጥቻቸዋለሁና፣ እነርሱም ተቀብለውታል"

"...ከአንተ እንደወጣሁ በእውነት አውቀዋል"

"ስለ እነርሱ እለምናለሁ... በእነርሱም እከብራለሁ"

"በእውነትህ ቀድሳቸው - ቃልህ እውነት ነው"

"አንተ የሰጠኸኝንም ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፣ እኛ አንድ እንደሆንን እነርሱም አንድ ይሆኑ ዘንድ"

"እኔም በእነርሱ፣ አንተም በእኔ፣ በአንድ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ"

መላው ምዕራፍ በጥንቃቄ መነበብ አለበት፣ እና እዚያ የተገለጸው እያንዳንዱ ሐሳብ በትኩረት ለመታየት ምክንያት ነው። እኛም ራሳችንን "ከእኔ ጋር እንደዚህ ነውን?" ብለን መጠየቅ አለብን። እነዚህ ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ፣ ማለትም፣ የዘላለም ሕይወት ካገኘን፣ ስሙ ለእኛ ከተገለጠልን፣ ቃሉን ከተቀበልን፣ በተገለጠው እውነት ከተቀደስን፣ አብ በክርስቶስ እንደኖረ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ከኖረ፣ ለዚህ አንድነት እጩዎች ነን እናም

በአንድ ፍጹም ልንሆን እንችላለን። እነዚህን ነገሮች በግልጽ ለማየት መለኮታዊ መገለጥ እና ለመለማመድ ጸጋ ይጠይቃል።

ጌታችን የጸለየለትን አንድነት ለማምጣት እግዚአብሔር የራሱ መንገድ አለው። ሁሉም እውነተኛ ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ ኢየሱስ በጸሎቱ የጠቀሳቸውን ነገሮችን ይለማመዳሉ። ከቃሉ ጋር በአንድነት ይሄዳሉ እናም እነርሱም ራስ ከሆነው ጋር አንድ ይሆናሉ፣ እናም የአካሉ አባላት እንደመሆናቸዉ እርስ በርስ አንድ ይሆናሉ። "በአንድ መንፈስ ሁላችን ወደ አንድ አካል ተጠመቀናን" (1ቆሮ.12፡13)።ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፣ "...የመንፈስን አንድነት በሰላም ማሰሪያ ትጠብቁ ዘንድ ትጉ። አንድ አካል፣ አንድ መንፈስ፣ በአንድ ተስፋም ተጠርታችኋልና። አንድ ጌታ፣ አንድ እምነት፣ አንዲት ጥምቀት፣ አንድ አምላክና የሁሉ አባት አለ፣ እርሱም ከሁሉ በላይ በሁሉ እና በሁላችሁም የሚኖር ነው።" (ኤፌ.4፡3-6)

አምስቱ አገልግሎቶች (ቁ.11) "ቅዱሳንን ፍጹም ለማድረግ... የክርስቶስን አካል ለመገንባታ ነዉ፤ ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ አንድ እስክንሆን ድረስ፤ፍጹም ሰዉ እስክንሆን ድረስ እና ፣ ወደ ክርስቶስ ሙላት መጠን እስክንደርስ ድረስ" (ቁ.11-13) ።

## ታሪክ ራሱን ይደግማል?

በክርስቶስ የመጀመሪያ ምጻአት የእግዚአብሔር ሕዝብ መሲሑን ለማየት በታላቅ መጠባበቅ(expectation) ውስጥ ነበሩ። በተመሳሳይ ጊዜ ከሃይማኖት መሪዎች አንዳቸውም ቀድሞ የመጣውን ሰውና አገልግሎቱን አላወቁም። የእግዚአብሔር ቃል በእጃቸው እያለና በቤተ መቅደስ ውስጥ እያመለኩ በኋላ ላይ መሲሑን አልተቀበሉትም ነበር። ለማመን የሚከብድ ቢሆንም እውነት ነው፡ እርሱ ወደ ገዛ ወገኖቹ መጣ፣ የገዛ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም (ዮሐ.1)። አንድ ሰው "በዚያ ዘመን በነበሩት በመንፈሳዊ ዕውርነት በተመቱ መሪዎች ሁሉ አፈርኩ !" ሊል ይችላል። እነርሱ የራሳቸው ትርጓሜዎች ነበራቸው እንጂ የቅዱሳት መጻሕፍት መገለጥ አልነበራቸውም።

ታሪክ ራሱን እየደገመ ይሆን? የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታችን እና የወንጌላዊነት ዘመቻዎቻችን የተለመዱ፣ መንፈሳዊ መዝናኛዎች ሆነዉ ይሆን? ስለ መሲሑና ወደፊት ስለሚያደርገው ነገር መስበክ፣ በተመሳሳይ ጊዜ አሁን እያደረገ ያለውን ችላ ማለት ይቻላል። በዚያ ዘመን የነበሩት የሃይማኖት መምህራን አብርሃምንና ሙሴን ይጠቅሱ ነበር፣ ነገር ግን እነርሱ የተናገሩት ነገር በመካከላቸው እውነት እንደሆነ አልተረዱም። ጌታችን "ሙሴንስ ብታምኑ ኖሮ እኔን ባመናችሁ ነበር" (ዮሐ.5፡46) ማለት ነበረበት።

ጴጥሮስንና ጳውሎስን፣ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የመረጥናቸውን ሰዎች መጥቀስ፣ እና እግዚአብሔር አሁን እያደረገ ያለውን ነገር አለመረዳት በእርግጥም ይቻላል። አንድ ጊዜ ደግሞ ራሳችንን መጠየቅ እንችላለን፣ "እነዚያ ቅዱሳን ሰዎች - ቀንና ሌሊት ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲያጠኑ የነበሩ - ሁሉም ትንቢቶች እንደተፈጸሙ እንዴት አላዩም?" ኢየሱስ በናዝሬት ከተማ መጽሐፍ ቅዱስን ሲከፍት፣ ከኢሳ.61 ላይ ካነበበ በኋላ፣ "**ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጽሟል**" (ሉቃስ 4፡21) የሚለውን ትኩረት የሚስብ መግለጫ ሰጠ።

ያለ ምንም ጥያቄ፣ አሁን የምኖረዉ በመጨረሻዉ ዘመን መጨረሻ ላይ ነው። ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ በፍጥነት የሚከሰቱ የፍጻሜው ዘመን ክስተቶችን ይጠብቃል። በእርግጥ፣ የዘመኑ ምልክቶች፣ የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ፣ የእስራኤል መሰብሰብ እና የፖለቲካዊ ለውጦች የጌታ መምጣት ቅርብ መሆኑን በግልጽ ያሳያሉ። እግዚአብሔር በአገልግሎቱ ያልተረዳና ውድቅ የተደረገ፣ አልፎ ተርፎም ከእርሱ ከፍተኛ ጥቅም ባገኙ ሰዎች ዘንድ ያልተቀበሉትን አገልግሎት ልኮ ይሆን?

ያለፈውን መፍረድ፣ ምን ስህተት እንደተሰራ መለየት እና ለወደፊቱ ተስፋዎችን ማዳበር ከባድ አይደለም፣ በተመሳሳይ ጊዜ ጌታ አሁን እያደረገ ያለውን ነገር አለማወቅ። በመጀመሪያ በአሞጽ 3፡7 ላይ የሚገኘውን ቁልፍ መግለጫ መረዳት አለብን፣ **"እግዚአብሔር አምላክ ምስጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ሳይገልጽ ምንም አያደርግም።"** አሁን በእርግጥም ከሁሉም ዘመናት ታላቁ በሆነው የትንቢታዊ ዘመን ውስጥ እየኖርን ነው። ታላቅ ኃላፊነት የነበራቸው ሁለት ልዩ ትውልዶች ነበሩ፡ ክርስቶስ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመጣ የነበረው ትውልድ፣ እና አሁን - የእኛ ትውልድ - ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ ከመምጣቱ በፊት። አዲስ ኪዳን ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት መፈጸም ሲጀምር ተጀመረ፣ እና በተመሳሳይ መንገድ ያበቃል።

እግዚአብሔር ምን ታላቅ ነገር እንዳዘጋጀ በራሱ ምናባዊ ሐሳቦች የሚተነብይ ሰው አያስፈልገንም። እነዚህ ምናባዊ ሀሳቦች አልተፈጸሙም እናም በፍጹም አይፈጸሙም። ለዚህ ዘመን የተሰጠዉን የተስፋውን ቃል ግልጽ የሆነ ግንዛቤ ያስፈልገናል። ይህ ትንቢታዊ ዘመን ስለሆነ፣ **የአንድ የዋና ነቢይ** አገልግሎት በእግዚአብሔር እቅድና መርሃግብር ዉስጥ ይገጥማል። ልዩ ክስተቶች ከመከሰታቸው በፊት፣ ጌታ ብዙውን ጊዜ እንደዚህ ያለ ልዩ ተልእኮ ያለው ሰው ልኮ ነበር። ከጥፋት ውሃ በፊት፣ እርሱ ኖኅ ነቢይ ነበረው፣ እርሱም "ኖኅም እንዲሁ አደረገ፣ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሁሉ እንዲሁ አደረገ" (ዘፍ.6፡22) የሚል እናነባለን። ሰዶምና ገሞራ ከመጥፋታቸው በፊት ጌታ ነቢዩ አብርሃምን ጎበኘ (ዘፍ.18)። በቁጥር 17 ላይ "እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፦ እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን?" የሚል እናነባለን። በሉቃስ 17፡26-30 ላይ ጌታ እነዚያን ዘመናት ጠቅሶ "የሰው ልጅ በሚገለጥበት ቀን እንዲሁ ይሆናል" ብሏል። እግዚአብሔር ሊለወጥ አይችልም። "እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ አልለወጥም" (ሚል.3፡6) ይላል። የእርሱ ውሳኔዎች ለዘላለም ፍጹም ናቸው። ሁልጊዜም በተመሳሳይ መንገድ ይሠራል። ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ ለመፈጸም (ዘፍ.15፡13) ሲዘጋጅ፣ በጫካ ውስጥ ለነቢዩ ለሙሴ ታየ። እርሱ ኤልያስና ኤልሳዕ፣ ኤርምያስና ዳንኤል፣ ኢሳይያስና ሕዝቅኤል እና ሌሎችም ነበሩት።

## ቃሉን በትክክል መከፋፈል

ከአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ ጀምሮ ሐዋርያው ጴጥሮስ ሁሉም ነገር በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት እንደተፈጸመ አሳይቷል። የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስን በተመለከተ ሲጠየቅ "ይህ በነቢዩ በኢዩኤል የተነገረ ነው" (ሐዋ.2፡16) አለ። በምዕ.3፡20-23 ላይ ከጌታ ፊት የሚመጣውን "የመጽናናት ጊዜ" ይናገራል። እርሱም ደግሞ "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በቅዱሳን ነቢያት ሁሉ አፍ የተናገረውን **ሁሉ ነገር እስከሚመልስበት** ዘመን ድረስ ሰማይ ሊቀበለው ይገባል" ብሎ ተናግሯል፣ ከዚያም ለእኛ የተሰበከው ኢየሱስ

ክርስቶስ ይመለሳል:: ቃላቶች ትርጉም ካላቸው፣ ይህ ማለት ኢየሱስ፣ ሙሽራው፣ የሚወዳትን ሙሽራዋን ወደ ቤቱ ከመውሰዱ በፊት፣ የነገሮች መመለስና የመጽናናት ጊዜ መጀመሪያ መምጣት አለበት ማለት ነው::

ያዕቆብ እንዲህ ሲል ጽፏል፣ "እንግዲህ፣ ወንድሞች ሆይ፣ ጌታ እስኪመጣ ታገሡ:: እነሆ፣ ገበሬው የከበረውን የምድር ፍሬ ይጠብቃል፣ የፊተኛዉንና የኋለኛዉን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ በትዕግስት ይጠብቃል::" (5:7) የመንፈስ ቅዱስ የመጨረሻ መፍሰስ ከመደረጉና አዝመራው ከመሰብሰቡ በፊት፣ በኢሳ.55:11 ላይ ያለው ቃል ከንቱ ሆኖ አይመለስም፤ ነገር ግን የተላከበትን ያከናውናል የሚለው ተስፋ ይፈጸማል:: በያዕ.5:11 ላይ ኢዮብ ያገኘው መመለስ እንደ ምሳሌ ተሰጥቷል:: ሁሉም ሰው ታሪኩን፣ የደረሰበትን መከራ፣ ሰይጣን በዙሪያው ያለውን ነገር ሁሉ እንዴት እንዳጠፋ፣ እና መጨረሻ ላይ እግዚአብሔር ሁለት እጥፍ እንዴት እንደመለሰለት (ኢዮብ 42:10) ያውቃል:: በመጀመሪያ እግዚአብሔር ምን ተስፋ እንደሰጠ(የገባዉን ቃል) ማወቅና ማመን አለብን፣ ከዚያም አስደናቂውን መመለስ በእዉነት ማየት አለብን::

የእግዚአብሔር ቃል ውድነት እጅግ ታላቅ ነው:: ስለ መጥመቁ ዮሐንስ አገልግሎት ስንናገር፣ አዘጋጅ የሚለው ቃል ሁልጊዜም ጥቅም ላይ ይውላል (ኢሳ.40:3፤ ሚል.3:1):: መልአኩ ገብርኤል የዮሐንስን መወለድ ሲያበስር "እርሱም የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፤የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ለመመለስ፣ ለጌታም የተዘጋጀ ሕዝብ ለማዘጋጀት በኤልያስ መንፈስና ኃይል ከፊቱ ይሄዳል" (ሉቃስ 1:17):: ዘካርያስ "አንተም ሕፃን ሆይ፣ የልዑል ነቢይ ትባላለህ፤ መንገዱንም **ለማዘጋጀት** ከጌታ ፊት ትሄዳለህና" (ሉቃስ 1:76) ሲል ተናገረ:: ጌታችን ይህንን በማቴ.11:10 ላይ አረጋግጧል፣ "እነሆ፣ መንገድህን በፊትህ የሚያዘጋጅ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተጻፈለት ይህ ነውና::"

ከዮሐንስ አገልግሎት ጋር ተያይዞ **"መመለስ"** የሚለው ቃል አንድ ጊዜ እንኳ ጥቅም ላይ አልዋለም:: በሌላ በኩል ደግሞ ለመጨረሻዉ ዘመን ቃል ከተገባዉ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ተደጋግሞ ይገኛል:: እግዚአብሔር በነቢዩ ኢዩኤል "ዓመታትን እመልስላችኋለሁ..." (ምዕ.2:25) አለ:: በማቴ.17 ላይ ስለ ተራራው መለወጥ ተሞክሮ እናነባለን:: ጌታችን ጴጥሮስን፣ ያዕቆብን እና ዮሐንስን ከእርሱ ጋር ወሰደ፣ እንዲሁም ሙሴና ኤልያስ ተገለጡና ከእርሱ ጋር ተነጋገሩ:: ጴጥሮስ እንደተለመደው በጣም ፈጣን ነበር እና "ጌታ ሆይ፣ ለእኛ እዚህ መሆን ጥሩ ነው፤ ብትወድስ ለእናንተ ሦስት ድንኳኖችን እንሥራ፤ አንዱን ለአንተ፣ አንዱን ለሙሴ፣ አንዱን ደግሞ ለኤልያስ" አለ::

ከተራራው ሲወርዱ ደቀ መዛሙርቱ ጌታችንን "ታዲያ ጸሐፍት ኤልያስ አስቀድሞ መምጣት አለበት የሚሉት ለምንድን ነው?" ብለው ጠየቁት:: ከዚህ በኋላ ጌታ ሁለት መግለጫዎችን ሰጠ:: የመጀመሪያው ስለወደፊቱ፣ ሁለተኛው ደግሞ ስለነበረው ስላለፈው ነበር:: የመጀመሪያው በቁ.11 ላይ ይገኛል፣ "ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው:- ኤልያስ በእርግጥ አስቀድሞ **ይመጣል፣** ሁሉንም ነገር ይመልሳል::" ምንም ጥርጥር የለዉም ፤ያ ጥቅስ የተነገረዉ በወደፊት ጊዜ ሲሆን፣ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት ያለዉን አገልግሎት ያመለክታል:: በዓለም አቀፍ ደረጃ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁርና ተርጓሚ በመሆን የሚታወቁት

ዶክተር ስኮፊልድ፣ በግርጌ ማስታወሻቸዉ ላይ **"ክርስቶስ የሚልክ.4፡5-6ን ልዩና ገና ያልተፈጸመ ትንቢት ያረጋግጣል"** ብሎ ጽፏል።

እንደተመለከትነው ዮሐንስ የሚል.3፡1 ነብይ እንደሆነ ተረጋግጧል። "አንተ ኤልያስ ነህን?" ተብሎ ሲጠየቅ፣ "እኔ አይደለሁም" (ዮሐ.1፡21) ብሎ መለሰ። ከዚህ መግለጫ በኋላ፣ በፈሪሳውያን የተላኩት ልዑካን "እንግዲያውስ ክርስቶስም ኤልያስም ያ ነቢይም ካልሆንህ ስለ ምን ታጠምቃለህ?" (ዮሐ.1፡25) ብለው ጠየቁት። የሚል.4 ትንቢት በአጭር ጊዜ ዉስጥ መፈጸም አለበት የጌታ ታላቅና ክፉ ቀን ከመምጣቱ በፊት - የበቀል ቀን(ኢሳ61፡2)፤ልክ እንደ ምድጃ የሚያቃጥል (ሚል.4፡1) እና እንደ ሌባ ሆኖ በሌሊት ይመጣል (2ጴጥ.3፡10፤ 1ተሰ.5፡2)።

ከዮሐንስ አገልግሎት ጀምሮ ወደ 2,000 ዓመታት አልፈዋል፣ የጌታ ቀን ግን ገና አልመጣም። የጌታን ቀን የሚገልጹ ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት አሉ። ፍላጎት የአለዉ አንባቢ ወደ ኢሳ.13፡6-13፣ ኢዩኤል 2፡30-31 እንዲመለከት ይመከራል። ጴጥሮስ በመጀመሪያው ስብከቱ ላይ "ታላቁና የተሰማው የጌታ ቀን ሳይመጣ ፀሐይ ወደ ጨለማ፣ ጨረቃም ወደ ደም ትለወጣለች" (ሐዋ.2፡20) ብሏል። ከጌታ ቀን ጋር የተያያዙ ክስተቶች በስድስተኛው ማኅተም (ራዕ.6፡12-17) ላይ ይገኛሉ፣ "...የቁጣውም ታላቅ ቀን መጥቷልና፣ መቆም የሚችል ማን ነው?" በእርግጥም በዚያ ጊዜ የምህረት ወንበር የፍርድ ወንበር ይሆናል።

በብሉይ ኪዳን የመጨረሻ ምዕራፍ በመጨረሻዎቹ ሁለት ቁጥሮች ላይ ኢየሱስ የጠቀሰውን ተስፋ እናገኛለን፡ "እነሆ፣ ታላቁና የሚያስፈራው የጌታ ቀን ሳይመጣ ነቢዩ ኤልያስን እልክላችኋለሁ። እኔም መጥቼ ምድርን በእርግማን እንዳልመታ፣ **የአባቶችን ልብ ወደ ልጆቻቸው፣ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶቻቸው ይመልሳል።**" የአባቶችን ልብ ወደ ልጆቻቸው የመመለስ የመጀመሪያው ክፍል በመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ተፈጽሟል። ገብርኤል ለዘካርያስ "በኤልያስ መንፈስና ኃይል ከፊቱ ይሄዳል፣ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆቻቸው ይመልሳል" (ሉቃስ 1፡17) ብሎ አረጋግጧል።

በዕብ.1 መሠረት፣ እግዚአብሔር በቀደሙት ጊዜያት በነቢያት ለአባቶች ተናግሯል። በመጨረሻም በልጁ ተናገረ። ልጁም መልሱ ነበር። ዮሐንስ ብሉይን ከአዲስ ኪዳን ጋር አገናኘ። በዚህም ምክንያት ከነቢይ የሚበልጥ ተብሎ ተነግሮለታል (ማቴ.11፡9)። ነቢያት ስለሚመጣው መሲሕ ተናገሩ። ዮሐንስ እርሱን የማስተዋወቅ መብት አገኘ። ኢየሱስ አገልግሎቱን በተደጋጋሚ ከሚል.3፡1 ጋር በማማይዝ ጠቅሷል። በማቴ.17፡12 ላይ ያለው "እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ኤልያስ ቀድሞ መጥቷል፣ እነርሱም አላወቁትም" የሚለው መግለጫ አስፈላጊ ነበር፣ ምክንያቱም ስለኤልያስ የተሰጠዉ የተስፋ ቃል የመጀመሪያው ክፍል ተፈጽሟል። እኛ የምንናገረው ስለ ሁለት ልዩ አገልግሎቶች ነው፡ አንዱ ከክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአት በፊት ፣ ሌላው ደግሞ ከሁለተኛዉ ምጽአቱ በፊት ነው።

በተለያዩ የመጻህፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ በአንድ እና በተመሳሳይ ጥቅስ ውስጥ የተለያዩ መምጣቶች እንደተጠቀሱ እናገኛለን። መዝ.2፡7-8፤ ሐዋ.13፡33፤ ዕብ.1፡5 ከመጀመሪያው መምጣት ጋር ይያያዛሉ። ሁለተኛው መምጣቱ ግን በዓለም ዘንድ አይታወቅም። በዚያን ጊዜም በደሙ የታጠበችውን (ራዕ.1፡5)፣ በቃሉ የነጻችውን (ኤፌ.5፡26)፣ በመንፈስ የታተመችውን (ኤፌ.4፡30) ሙሽራ-ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ቤቱ (1ተሰ.4፡13-18) ለሰርጉ

እራት (ራዕ.19፡1-9) ይወስዳል፡፡ የተቀሩትም ስለ እርሱ አያውቁም፡፡ መዝ.2፡9፤ ራዕ.2፡27፤ 12፡5 እና ሌሎችም ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት ጠላቶቹን ለመጨረስና በምድር ላይ ንግሥናውን ለመጀመር በታላቅ ኃይል ስለመምጣቱ ይናገራሉ፡፡ በሉቃስ 4፡19 ላይ ኢየሱስ ከኢሳ.61 ሲያነብ በሁለተኛው ጥቅስ መካከል አቆመ፣ ምክንያቱም የመጀመሪያው ክፍል ብቻ ለዚያን ጊዜ ለአገልግሎቱ ይሠራ ነበር፡፡ የቁጣ ቀን የምህረት ጊዜ ሲያልፍ ይመጣል፡፡ ከዚህ በፊት እንደተገለጸው፣ ሚል.3፡1 ከመጀመሪያው መምጣት ጋር ይያያዛል፣ እናም አውዱ እንደሚያሳየው፣ ሚል.4፡5-6 ከሁለተኛው መምጣት ጋር ይያያዛል፡፡

## በጣም አስፈላጊ

አሁን ያለው ተልእኮ **የእግዚአብሔርን ልጆች ልብ** ወደ ሐዋርያት አባቶች እምነት መመለስ ነው፡፡ ለዚህ ከእግዚአብሔር የተላከ ሰው - እንደ ኤልያስ ያለ ነቢይ፣ ምንም ጥርጥር የሌለበት ማረጋገጫ ያለው ሰው ይጠይቃል፡፡ እርሱ የግድ ሁለት ነገሮች ሊኖሩት ይገባል፡ ለሰዓቱ የተገባዉ ቃል እና እውነተኛ የተመለሰ ሐዋርያዊ አገልግሎት፡፡ ይህ ደግሞ የእርሱን ቀጥተኛና ልዩ ተልእኮውን አሳማኝ ማረጋገጫ ይሆናል፣ በዚህም የእግዚአብሔር ሕዝብ ትኩረት ወደ ሰዓቱ መልእክት ይሳባል፡፡

ስለ ኤልያስ የተሰበረዉን የእግዚአብሔርን መሠዊያ እንደገና እንደሰራ እናውቃለን፡፡ ይህንንም ለማድረግ አስራ ሁለቱን ድንጋዮችን እንደ አስራ ሁለት ነገዶች ወስዶ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለውሳኔ ጠራ፡፡ "እኔም የአንተ አገልጋይ ነኝ፣ ይህንም ሁሉ በቃልህ አድርጌአለሁ" ማለት ይችላል፡፡ በጸሎቱ ውስጥ "አቤቱ፣ ስማኝ፤ ይህ ሕዝብ አንተ እግዚአብሔር እንደሆንህ፣ **ልባቸውንም እንደ መለስክላቸው ያውቁ ዘንድ ስማኝ**" (1ነገሥት 18፡37) ብሏል፡፡ የመጀመሪያው ኤልያስ እና በኤልያስ መንፈስ የመጣው መጥመቁ ዮሐንስ ፣ እንዲሁም የዛሬው "ኤልያስ" አንድ የጋራ ነገር አላቸው፡ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ልብ ወደ ቃሉ መመለስ፡፡

በመጨረሻው አገልግሎት፣ የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ትምህርት መመለስ እና የእግዚአብሔር ሕዝብ ልብ ወደ እርሱና ወደ ቃሉ መመለስ አለበት፡፡ እውነትን ለማይወዱት ሁሉ ሐሰትን እንዲያምኑ ለጠንካራ ማታለል ተላልፈዉ ተሰጥተዋል (2ተሰ.2፡11)፡፡ "እውነትንም ከመስማት ጆሮአቸውን ይመልሳሉ፣ ወደ ተረትም ይመለሳሉ" (2ጢሞ.4፡4)፡፡ በእያንዳንዱ እንግዳ ትምህርት ነፋስ መወዛወዝ በእዉነት ለተመለሱት ያበቃል፡፡ እነርሱ ከባቢሎን ካምፖች ተጠርተው ጤናማውን ትምህርት ይቀበላሉ (ቲቶ.2፡1)፡፡

ዮሐንስ ከእርሱ ጋር የተያያዙትን ቅዱሳት መጻሕፍት በትክክል እንዳወቀ፣ ይህ የመጨረሻዉ ዘመን ነቢይ ለሰዓቱ የተሰጠዉን የተስፋውን ቃል በመለኮታዊ መገለጥ ማወቅ አለበት፣ ትንቢትንም ጨምሮ፣ ጴጥሮስ እንደገለጸው፣ "ከዚህም ይልቅ የታመነ የትንቢት ቃል አለን…" (2ጴጥ.1፡19) እና የትንቢት መንፈስም ሊኖረው ይገባል፣ ዮሐንስ በጳጥሞስ ደሴት እንደተነገረው፣ "እኔ ከአንተ ጋር የኢየሱስ ምስክርነት ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፡፡ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ የኢየሱስ ምስክርነት የትንቢት መንፈስ ነውና" (ራዕ.19፡10)፡፡ የትንቢት መንፈስ ከትንቢት ስጦታ ጋር የተገናኘ አይደለም፣ ይልቁንም ከትንቢት ቃል ጋር የተገናኘ ሲሆን የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነት ነው፡፡ መላው ጉዳይ

በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ማንም ሰው በግምት ወይም በስሜት መሄድ አይችልም። በመጨረሻም እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ተግባሯን ታውቃለች፣ በተሰጣት ተስፋ ላይ ትቆማለች እና ከእርሱ ጋር አንድ ትሆናለች። ይህ በመንፈስ እውነተኛ አንድነት ይሆናል!

## እውነተኛ ነቢያት

ነቢያት ከእናታቸዉ ማህፀን ጀምሮ ለተወሰነ ዓላማ እና አገልግሎት የተሾሙ ናቸው (ኤር.1፡5)። መጀመሪያ ላይ ራእይ ስለሚያዩ "ባለ ራእዩች" ተብለው ይጠሩ ነበር (1ሳሙ.9፡9፣ 18፣ 19)። ራዕይን ሲያዩ መነሳሳትን ይቀበሉ ነበር፣ በዚህም ከእግዚአብሔር መገለጥን ያመጡ ነበር (ኤር.1፡11+12)። የእግዚአብሔር ቃል ሁልጊዜም ለነቢያት ይመጣ ነበር፣ "እርሱም እንዲህ አለ፡- ቃሌን ስሙ፤ በእናንተ ዘንድ ነቢይ ካለ እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገልጽለታለሁ፣ በሕልምም እነግረዋለሁ" (ዘኍ.12፡6)። እውነተኛ ነቢይ የእግዚአብሔር አፍ ነው። እንደ ዮሐንስ እና እንደሌሎቹም ለዘመኑ "ጌታ እንዲህ ይላል" የሚል ያስፈልገው ነበር። እንደዚህ ያለውን ነቢይ የሚቀበሉ እና አገልግሎቱን የሚቀበሉ ሁሉ የነቢይን ዋጋ ይሰጣቸዋል (ማቴ.10፡41)። ጌታ ራሱ "በነቢያቶቼ ክፉ አታድርጉ" (1ዜና.16፡22፤ መዝ.105፡15) ብሏል።

የብሉይ ኪዳን ነቢያት እስከ ዮሐንስ ድረስ ነበሩ፣ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰበካል (ሉቃስ 16፡16)። ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን ዘመን ነቢይ አይኖረውም የሚለውን ሀሳብ ለመከላከል አንዳንድ ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላል። ነገር ግን ዮሐንስ ራሱ ነቢይ ነበር፣ ስምዖንም ነቢይ ነበር፣ እና ጌታችን ኢየሱስ "ስለዚህም እነሆ፣ ነቢያትን፣ ጥበበኞችንና ጻፎችን ወደ እናንተ እልካለሁ…" (ማቴ.23፡34፤ ሉቃስ 11፡49) የሚል ተስፋ ሰጥቷል። እዚህ ላይ "ጻፎች" የሚለው ቃል በእርግጥም በገማልያል እግር ሥር ተቀምጦ የነበረውን ሰው አያመለክትም። "እርሱም እንዲህ አላቸው፡- ስለዚህ የመንግስተ ሰማያት ደቀ መዝሙር የሆነ ጻፊ ሁሉ ከመዝገቡ አዲሱንና አሮጌዉን የሚያወጣ ባለቤትን ይመስላል አላቸዉ" (ማቴ.13፡52)።

የሐዋርያት ሥራን የሚያነብ ማንኛውም ሰው በተለያዩ ነቢያት የሚሰጠውን የአገልግሎት ዱካ በቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ያገኛል (ምዕ.13)። በምዕ.15፡32 ላይ "ይሁዳና ሲላስ ነቢያት ነበሩና…" የሚል እናነባለን። በ1ቆሮ.14 ላይ ጳውሎስ አገልግሎቶችን ያስቀምጣል እና በመጨረሻም "አንድ ሰው ነቢይ እንደሆነ ወይም መንፈሳዊ እንደሆነ ቢያስብ፣ የምጽፍላችሁ የጌታ ትእዛዝ እንደሆነ ይውቅ" (ቁ.37) ብሎ ይናገራል። በኤፌ.3 ላይ ጳውሎስ ስላገኘው መገለጥ ጽፏል። ስለ ክርስቶስ ምስጢር ሲናገር "አሁን ለቅዱሳን ሐዋርያትና ነቢያት በመንፈስ እንደተገለጠ፣ በሌሎች ትውልዶች ለሰው ልጆች አልታወቀም ነበር" (ቁ.5)። በኤፌ.4፡11 እና በ1ቆሮ.12፡28 ላይ የነቢይነት ቢሮ በእግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተቀመጡት የተለያዩ አገልግሎቶች ውስጥ ተካትቷል። **የመዳን እቅድ ትንቢታዊው ክፍል ዋና ነቢይን ይጠይቃል።**

ታሪክን የሚያውቁ ሁሉ ቀደም ብሎ መሐመድ እና ሌሎች በርካታ ሰዎች ከጌታ ታላቅና ክፉ ቀን በፊት ሊመጣ ያለውን የሚልክ.4፡5 ላይ የተጠቀሰውን ነቢይ እንደሆኑ ተናግረዋል። በእርግጥም፣ አንዳንዶች ራሳቸውን "ኤልያስ" ብለው በግልጽ ጠርተው ወይም ስለ "ኤልያስ

አገልግሎት" ተናግረዋል። ነገር ግን ከእነርሱ አንዱም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ልብ ወደ ጌታና ወደ ቃሉ አልመለሰም። በተቃራኒው፡ እነርሱ ራሳቸው ከእውነተኛው የሐዋርያዊና የትንቢት ትምህርት የራቁ ነበሩ እና የራሳቸውን ተከታዮች አፍርተዋል። ሆኖም፣ እነዚህ ሁሉ አስመሳዮች እግዚአብሔር በተገቢው ጊዜ ቃሉን እንዳይፈጽም አያግዱትም።

## ፈተና(challenge)

መጽሐፍ ቅዱስን በማወቅ እና እግዚአብሔር በቀደሙት ጊዜያት እንዴት እንደሠራ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አሁን ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ነገር እንዲያደርግ መጠበቅ አለብን። መረጃዬ ትክክል ከሆነ፣ እግዚአብሔር ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የጀመረውን የአሁኑን የመነቃቃት(ሪቫይቫል) እንቅስቃሴ ለመምራት የመረጠውን ሰው ተጠቅሟል። በአገልግሎቱ የማይታመኑ ነገሮች በትክክል በመድረክ ላይ ተከሰቱ። ዓይነ ስውሮች ማየት ቻሉ፣ ሽባዎች መራመድ ቻሉ፣ ዲዳዎች መናገር ቻሉ፣ ደንቆሮች ወዲያዉኑ መስማት ቻሉ። በ1950 በሚች ሬቨርንድ ጎርደን ሊንሳይ የተጻፈው "ከእግዚአብሔር የተላከ ሰው" በተሰኘዉ መጽሐፍ፣ በወቅቱ ""ዘ ቮይስ ኦፍ ሂሊንግ"" የተሰኘዉ መጽሔት አዘጋጅ በነበሩበት ጊዜ እና በ1952 በሬቨርንድ ጁሊየስ ስታድስክሌቭ የታተመው "ነቢይ ደቡብ አፍሪካን ጎበኘ" በተሰኘዉ መጽሐፍ፣ እንዲሁም በቴክሳን አሪዞና በሚኖሩት በሬቨርንድ ፔሪ ግሪን የተጻፈው "የነቢዩ ሥራዎች" በተሰኘዉ መጽሐፍ እና በተለያዩ ሌሎች ጽሑፎች ውስጥ አስደናቂ ነገሮች ተመዝግበዋል። አልፎ ተርፎም ተስፋ የሌላቸው የካንሰር ታካሚዎች ተፈውሰዋል እናም የመፍጠር ተአምራት ተከሰቱ። እ.ኤ.አ. ግንቦት 7፣ 1946 ለአርሱ ልዩ ተልእኮ እንደተሰጠው እንኳ እናነባለን።

ለዓመታት የተለያዩ ሪፖርቶች በአሜሪካ መጽሔቶች ውስጥ ታትመው ነበር፣ ለምሳሌ "ሄራልድ ኦፍ ሆፕ"፣ "ዘ ቮይስ ኦፍ ሂሊንግ" - በኋላ " ክርስቶስ ፎር ዘ ኔሽንስ" ተብሎ ተሰይሟል - እና በሌሎችም ውስጥ። የዚህ መንፈሳዊ ሪቫይቫል ትክክለኛ መነሳሳት የተጀመረው ሌሎች ወንጌላውያን (በኋላ ታዋቂ የሆኑ) ወደ መድረክ ከመምጣታቸው በፊት ነበር። በእርግጥም፣ በአርባዎቹ መጨረሻ፣ በሃምሳዎቹ እና በስልሳዎቹ መጀመሪያ ላይ የጀመሩት የተወሰኑ ስብሰባዎች ላይ ተገኝተው መነሳሳትን እንደተቀበሉ አምነዉ መቀበል አለባቸው። በእርግጥም ይህንን አይቀበሉም፤ ይልቁንም ሁሉንም ዓይነት አስደናቂ ታሪኮችን ይፈጥራሉ።

የዚህ ሰው አገልግሎት የግል ምስክር እንደመሆኔ - ከብዙዎች መካከል - ያየሁትና የሰማሁት ተጽዕኖ ከማብራሪያ በላይ እንደነበር ልናገር እችላለሁ። በመቶዎችና በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እስከ ታህሳስ 1965 ድረስ አስካለዉ የአገልግሎት መጨረሻ ላይ በስብሰባዎች ዉስጥ የማይሳሳት የመለየት ስጦታንና መለኮታዊ እውቀትን አይተዋል። ምንም ሀገር፣ አህጉር እና ቋንቋ ሳይለይ፣ ይህ ትሑት ሰው ክፍት በሆነ ራዕይ ግለሰቡ ማን እንደሆነ፣ ምን በሽታ እንዳለበት፣ ከየት እንደመጣ - ከተሞችን፣ ጎዳናዎችን እና የግለሰቦችን ስም ጭምር ያይ ነበር። እያንዳንዱ ራዕይ ሁልጊዜ ፍጹም ነበር፣ ለብዙ ዓመታት በዓለም ዙሪያ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ አንድም ራእይ ዉድቅ አልተደረገም። ከእውነተኛ ነቢይ አገልግሎት ጋር መለየት ያለባቸው ሁለት ባህሪያት አሉ፡ አንደኛ፣

የሚናገረው ነገር መፈጸም አለበት (ዘዳ.18፡20-22)፣ እና ሁለተኛ፣ ስለ እግዚአብሔር የሚያስተምረው ትምህርት ትክክል መሆን አለበት። ሰውየው የሚናገረው ነገር ከተፈጸመ፣ ነገር ግን በአብርሐም፣ በይስሐቅና በያዕቆብ አምላክ ፈንታ ሌሎች አማልክትን ካቀረበ አሁንም ሐሰተኛ ነቢይ ነው፣ እና እግዚአብሔር ሕዝቡን እየፈተነ ነው (ዘዳ.13፡2-6)።

ኢየሱስ እንደ ሰው ልጅ፣ "ነቢዩ" ነበር (ዘዳ.18፡15-19፤ ሐዋ.3፡22-23)፣ ስለዚህ በራዕይ አማካኝነት አብ ሊያደርግ ያለውን ነገር አየ። ከዚያም በአየዉ መሠረት አደረገ (ዮሐ.5፡19)። ጴጥሮስን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያገኘው "አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህ" አለው (ዮሐ.1፡40-42)። ፈጽሞ የማያውቀውን ናትናኤልን "ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ ዛፍ በታች ሳለህ አየሁህ" (ዮሐ.1፡43-49) አለው። በያዕቆብ የውሃ ጉድጓድ የነበረችው ሴት "አምስት ባሎች ነበሩሽ፣ አሁን ያለሽውም ባልሽ አይደለም" (ዮሐ.4፡5-30) ሲላት በጣም ተገረመች። ኢየሱስ የልብን ሐሳብ ሁሉ ያውቅ ነበር - እያንዳንዱ ምስጢር ለእርሱ ተገለጠ። በዚህ ትንቢታዊ አገልግሎት ምክንያት፣ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን እርሱን ብዔል ዘቡል ነዉ ብለዉ በጥንቆላና በአእምሮ በማንበብ ከሰሱት።

ይህ ከእግዚአብሔር የተላከ ሰው፣ ዊሊያም ብራንሃም፣ የተጠቀሱትን ቅዱሳት መጻሕፍት ደጋግሞ ይጠቅሳል። ስብከቱን ከሰበከ እና ለንስሃ ከጠራ በኋላ ለበሽተኞች ይጸልይ ነበር። እግዚአብሔር ሊያደርግ ያለውን በራዕይ እስኪያይ ድረስ ይጠባበቅ ነበር። በዚሁ መሠረት ይናገራል እና ይጸልያል። በመቶዎች የሚቆጠሩ አገልግሎቶች በቴፕ ተቀርጸዋል እናም እዚህ የተገለጹትን ነገሮች ማረጋገጥ ለሚፈልግ ለማንኛውም ሰው አሳማኝ ምስክርነት ናቸው።

እርሱ ሊጸልይለት ባለበት ሰው ላይ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ብርሃን ሲወርድበት በትክክል አየ። ይህ ብርሃን ለመጀመሪያ ጊዜ ፎቶግራፍ የተነሳው እ.ኤ.አ. ጥር 24 ቀን 1950 በሂውስተን ኮሊሰም በተደረገ ዘመቻ ወቅት ነበር። የማያምኑ እና ተቺ የሆኑ የጋዜጣ ፎቶግራፍ አንሺዎች እርሱን ለመወንጀል በማሰብ በፊልሙ ላይ የእግዚአብሔር አገልጋይ ራስ ላይ ይህ የብርሃን ሃሎ ሲታይ በጣም ተገረሙ።

ነቢዩ ሕዝቅኤል "የሽኪና ክብርን" ብዙ ጊዜ አይቷል (ሕዝ.1፡28፤ 3፡12+24፤ 10፡4+18)። ሳውልም ወደ ደማስቆ በሚወስደው መንገድ ላይ ተመሳሳይ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ብርሃን አገኘና "ጌታ ሆይ፣ ማን ነህ?" ብሎ ጠየቀ። እርሱም "የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ" (ሐዋ.26፡15) አለው። በእስራኤል ጉዞ ሁሉ ጌታ በቀን ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ደመና ውስጥ፣ በሌሊት ደግሞ በእሳት ዓምድ ውስጥ ከእነርሱ በላይ ነበር። እግዚአብሔር ብርሃን ነው እና በብርሃን ውስጥ ይኖራል። ኢየሱስ ብርሃን ሆኖ ወደዚህ ዓለም መጣ። ጌታ ለዘላለም አንድ ነው።

እ.ኤ.አ. የካቲት 28 ቀን 1963፣ ከተፈጥሮ በላይ የሆነው ደመና በአሪዞና ተራሮች ላይ ወርዶ ነበር፣ በትክክል ይህ የእግዚአብሔር ሰው በነበረበት ቦታ ላይ። ከዚያም ለተለየ አላማ የራዕይ መጽሐፍን ሰባት ማኅተሞች ለመስበክ ወደ ቤቱ ቤተ ክርስቲያን እንዲመለስ ተነግሮታል። ለሰባት ተከታታይ ቀናት፣ ከመጋቢት 17 እስከ 24 ቀን 1963 ድረስ፣ ያ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ብርሃን በየቀኑ በክፍሉ ውስጥ ያንጃብብ ነበር፣ እናም ስለሚናገርበት እያንዳንዱ ማኅተም በመለኮታዊ መንገድ ይገለጥለት ነበር። ይህንን ሁሉ ስንመለከት፣

ራሳቸውን "የሰዓቱ የእግዚአብሔር ሰው" "የእግዚአብሔር የመጨረሻዉ ዘመን ነቢይ" እና ሌሎችም ብለው የሚጠሩት እግዚአብሔር ያደረገውን እንዴት ማወቅ ወይም አለማወቅ እንዳልቻሉ ለመረዳት ይከብዳል።

እ.ኤ.አ. ሰኔ 11 ቀን 1933፣ በአሜሪካ ኢንዲያና በጄፈርሰንቪል በኦሃዮ ወንዝ ውስጥ በጥምቀት አገልግሎት ወቅት፣ አንድ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ነገር ተከሰተ። አራት ሺህ ያህል ሰዎች ነበሩ፣ እና በመቶዎች የሚቆጠሩ እየተጠመቁ ነበር፣ ይህ ብርሃን በእርሱ ላይ ሲወርድ እና አንድ ድምፅ " **መጥመቁ ዮሐንስ የክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአትን ቀዳሚ ሆኖ እንደተላከ፣ አንተም የክርስቶስ ሁለተኛ ምጽአቱን የሚቀድም መልእክት ይዘህ ተልከሃል"** አለ። ሌሎችም ብዙ አስደናቂ ክስተቶች ሊዘረዘሩ ይችላሉ።

በሰው ተጽዕኖ ሊደረጉ በማይችሉ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ውስጥ በሆኑ ነገሮች ፊት ለፊት ከተገናኘን፣ ገለልተኛ ሆነን መቆየት አንችልም፣ ነገር ግን ውሳኔ ማድረግ አለብን። ግዴለሽነት በእርግጥም መልስ አይደለም። እግዚአብሔር የሚያደርገው ማንኛውም ነገር ዓላማ አለዉ። በጌታ ዘመን እንደነበረው ሁኔታ ራሳችንን አግኝተን፣ እግዚአብሔር ምንም ልዩ ነገር እንዳላደረገ አድርገን በተለመደው አገልግሎታችን መቀጠል እና "ኤልያስ አስቀድሞ መምጣት የለበትም? ነቢይ መነሳት የለበትም?" ብለን መጠየቅ ይቻላልን? ዛሬም ተመሳሳይ መልስ ይሰጠን ነበር፣ "እርሱ ቀድሞ መጥቶ ሄዷል፣ እናንተ ግን አላወቃችሁትም እናም እንደፈለጋችሁ አደረጋችሁበት።" በዘመናችን ከአምላክ የተላከ ሰው እንደነበረ እውነት ከሆነ (እኔም እንደዚያ እንደሆነ አውቃለሁ)፣ ነገር ግን የመጎብኘት ቀናችንን ካላወቅን፣ በቀላሉ ታውረናል እናም ተሳስተን ሊሆን ይችላል። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያለውን የሰዓቱን እውነተኛ መልእክት እስክናገኝ ድረስ በሙሉ ሐቀኝነት ቅዱሳት መጻሕፍትን መመርመር የለብንም?

እንደተለመደው፣ ቤተ ክርስቲያኖችና የቤተ ክርስቲያን መመምህራን በራሳቸው መንገድ ውስጥ ቆይተው፣ እግዚአብሔር ያደረገውን እንደ ደስ የማይል ረብሻ አድርገው በመቁጠር፣ የጠላት ሥራ እንደሆነ አውጀው ሊሆን ይችላል። በስላሴ የሚያምኑት "ይህ ሰው 'አንድን' " ከሚያምኑት ነዉ ሲሉ፣ "አንድን " የሚያምኑት ደግሞ "እርሱ የስላሴ አማኝ ነው" አሉ። በሁለቱም ወገኖች ውስጥ ጥቂቶች ብቻ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው እንደሆነ አውቀውታል። እርሱ ከሁለቱም ወገን አልቆመም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሙሉ ምክር ሰበከ። እግዚአብሔር በሰማይ እንደ አብ፣ በምድር ላይ እንደ ወልድ፣ እና በተቤዣቸዉ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚኖር በግልጽ ገልጿል። እርሱም ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር አቋም ወስዷል እንዲህ እንዳጠቃለለው "አምላክን የመምሰል ምሥጢርም ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤ እርሱ በሥጋ ተገለጠ፣ በመንፈስ ጸደቀ፣ በመላእክትም ታየ፣ በአሕዛብ ዘንድ ተሰበከ፣ በዓለም ታመነበት፣ በክብርም ዐረገ" (1ጢሞ.3፡16)።

አልፎ ተርፎም በዚህ የጌታ ትሑት አገልጋይ አገልግሎት መነሳሳትን ያገኙ ወንጌላውያን - እና ከእርሱ ከፍተኛ ጥቅም ያገኙ ቤተ ክርስቲያኖች - የዚህን የመጨረሻው የመንፈስ እንቅስቃሴ በእግዚአብሔር የተወሰነዉን ዓላማ ላይረዱ ይችላሉ። እኛ ለዛሬው የእግዚአብሔር የመዳን እቅድ ጋር በእውነት ተዋውቀናል። አማኞች ከቃል ጋር ይስማማሉ፣ ምክንያቱም እነርሱ ራሳቸው፣ ይስሐቅ እንደነበረው፣ የተስፋ ልጆች ናቸው (ገላ.4፡28)፣ እና ልጆች ስለሆኑ የአብን ተስፋ ይቀበላሉ (ሐዋ.1፡4)።

ሆኖም፣ በአጠቃላይ፣ ጌታችን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመጣ እንደነበረው ተመሳሳይ ሁኔታ እናገኛለን። በተለይም የቤተ ክርስቲያን መምህራን፣ በተለያዩ ምክንያቶች፣ በ1977 የዓለም ሥርዓቶች እንደሚጠናቀቁ እና የሺህ ዓመቱ እንደሚጀመር እንደተነገረ በሚገመተው ጥቅሶች ላይ ይጠቅሳሉ፣ ይህም "የሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ትንታኔ" በተባለው መጽሐፍ ገጽ 322 ላይ ይገኛል። የተጠቀሰው ከቴፕ-የተቀዳ ስብከት በቀላል ንባብ ሬቨረንድ ብራንሃም እንደዚህ ያለ መግለጫ ፈጽሞ እንዳልሰጠ በግልጽ ያሳያል። እነዚህ የቤተክርስቲያን መምህራን - የማሰብ ችሎታ እንዳላቸው በማመን - እውነታዎችን ለማረጋገጥ ለምን አይጨነቁም? ከርሱ ጋር የማይገናኙ ሌሎች ብዙ ነገሮች ሰዎችን ለማስፈራራት ተሰራጭተዋል። በሌሎች ተጽእኖ ስር ያልወደቀ ማንኛውም ሰው ይህ የእግዚአብሔር ሰው በመለኮታዊ መገለጥ አማካይነት የቅዱሳት መጻሕፍት ጥልቅ ግንዛቤ እንደነበረው አምኖ ይቀበላል። አዎን፣ በቃል ውስጥ ያሉ ሁሉም የተደበቁ ምስጢሮች ወደ ብርሃን መጡ፣ እናም ለዚህም ጌታን አመስጋኞች ነን።

ምናልባትም ይህ ትሑት ትንታኔ አንዳንዶችን ከራሳቸው መንገድና ፕሮግራሞች ውስጥ እንዳይቀጥሉ ለማስገደድ እና የእርሱ የመጨረሻዉ ዘመን እቅድ አካል በመሆን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ታስቦ ሊሆን ይችላል። ምናልባት አንዳንዶች በሐሰተኛ "ማስረጃ" ስላመኑ ከእግዚአብሔር የተላከውን አገልግሎት ውድቅ አድርገው ሊሆን ይችላል፣ ሌሎች ደግሞ አክራሪ ሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተደገፉ ብዙ ነገሮችን እና የመልእክቱን ትርጓሜዎችን በመስጠት በመልእክተኛው ላይ ነቀፌታ አምጥተዋል።

ሁሉም ሰው ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲመረምር እና ሁሉንም ትምህርቶች በእግዚአብሔር ቃል እንዲያረጋግጥ ተጋብዟል። በራስህ ማስተዋል አትመካ፣ በሐሰተኛ ወሬዎችም አትመን። "እነዚህም የነበሩት ሰዎች… ቃሉን በሙሉ ፈቃደኝነት ተቀብለው፣ ነገሮች እንደዚያ እንደሆኑ ለማረጋገጥ በየቀኑ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይመረምሩ ነበር" (ሐዋ.17፡11)።

## የግል ምስክርነት

የዚህ ብሮሹር ጸሐፊ እንደመሆኔ መጠን በመጨረሻ ጥቂት ነገሮችን ለመናገር ተገፋፍቻለሁ፣ በጸሎት ዉስጥ ተሁኖ እንደሚታዩ ተስፋ በማድረግ።

ገና በወጣትነቴ ከጌታዬ ጋር ለመተዋወቅ ልዩ እድል አግኝቻለሁ። ከ1949 ጀምሮ እግዚአብሔር በዚህ ሰው አማካኝነት ስለሚያደርገው ታላቅ ነገር ከአሜሪካ ሰባኪዎች ሰማሁ። በአውሮፓና በአሜሪካ ውስጥ በተደረጉ የመንፈሳዊ ሪቫይቫል እና የፈውስ ዘመቻዎች ላይ ለመገኘት የተቻለኝን አጋጣሚዎች ተጠቅሜያለሁ። እ.ኤ.አ. በነሐሴ 1955 በጀርመን ውስጥ በዊሊያም ብራንሃም የተደረገ የአንድ ሳምንት ዘመቻ ላይ ተገኝቼ ነበር፣ ይህም በመንፈሳዊ ህይወቴ ላይ የማይረሳ ተጽዕኖ አሳድሯል። ለእኔ ለውጥ የሆነው ነጥብ እ.ኤ.አ. በሰኔ 1958 በዳላስ፣ ቴክሳስ በተደረገው "ቮይስ ኦፍ ሂሊንግ" ስብሰባ ላይ ነበር። በቀን በተደረጉ ስብሰባዎች ላይ የተለያዩ ወንጌላውያን ይሰብኩ ነበር። ምሽቶች ላይ ይህ ከእግዚአብሔር የተላከ ትሑት ሰው ዋና ተናጋሪ ነበር። በጀርመንና በአሜሪካ ባየኋቸው ብዙ አገልግሎቶች ውስጥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ፣ የመሲሑ ምድራዊ አገልግሎት ጋር ቀጥተኛ ተመሳሳይ ነበረ።

እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 2 ቀን 1962 ጎህ ሲቀድ ቃሉን እንድሰብክ ከእግዚአብሔር የጥሪ ድምጽ በግልጽ ሰማሁ፣ ይህ ደግሞ በዚሁ ዓመት ታህሳስ 3 ቀን በሬቨረንድ ብራንሃም በሁለት ምስክሮች ፊት ተረጋግጧል። በዚህ መንገድ አገልግሎቱ ከእርሱ ጋር በቀጥታ የተገናኘ

ነው። ከ20 ዓመታት በላይ በብዙ የእስያ፣ የአፍሪካ እና የምስራቅ አውሮፓ አገሮች ውስጥ ካሳለፍኩ በኋላ፣ እግዚአብሔር ስላደረጋቸው ነገሮች ሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያወቅበት ጊዜ ደርሷል ብዬ አስባለሁ። እግዚአብሔር ሬቨረንድ ብራንሃም የክርስቶስን ሁለተኛ ምጽአት እንደሚቀድም አልተናገረም፣ ነገር ግን **"የሁለተኛ ምጽአቱን የሚቀድም መልእክት ይዘህ ተልከሃል" ተብሎ እንደተነገረው** አስታውሱ። እግዚአብሔር መልእክተኛውን ወሰደው፣ መልእክቱን ግን ከእኛ ጋር ትቶ ሄዷል። ይህ መልእክት ለአሁን ጊዜ እግዚአብሔር ቃል የገባዉ እና የተገለጠ ቃል ነው። እንደ ምስክርነት ለሁሉም ሕዝቦች ሊሰበክ ከሚገባው የዘላለሙ ወንጌል ክፍል ነው (ማቴ.24፡14፤ ራዕ.12፡6)። ሙሉው ወንጌል የመጨረሻዉ ዘመን ትንቢታዊ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያካትታል።

አሁን ዕብ.13፡8፣ ዮሐ.14፡12፣ ማር.11፡22 እና ሌሎች ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚረጋገጡበት የመጨረሻው ምዕራፍ ውስጥ እየገባን ነው። እነዚህ ሬቨረንድ ብራንሃም ደጋግሞ ይጠቅሳቸው የነበሩ ሶስት ተወዳጅ ጥቅሶች ነበሩ። ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን በኋላ ማንም ያላየዉን እነርሱ በትክክል ሲፈጸሙ አይቷቸዋል። ሁሉም ነገር ከእግዚአብሔር የጽሑፍ ቃል ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማማ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን። ጥያቄው እንደዚህ ያለውን ሰው እንቀበል ወይም አንቀበል የሚለው ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ያደረገውን እንቀበል የሚለው ነው። ጌታ ራሱን እንደገና በቀላል መንገድ ከገለጠበት እውነታ ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጠናል። በፍርድ ቀን ለእርሱ እንጂ ለሰው መልስ አንሰጥም። እንደዚህ ያለ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ማረጋገጫ በተፈጸመበት ቦታ፣ ሁሉም በሰው የተፈጠሩ ክርክሮች ከንቱ ይሆናሉ ።

**በዚህ የመጨረሻዉ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ከእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል የመጣው መልእክት የክርስቶስን ሁለተኛ ምጽአት እንደሚቀድም እርግጠኛ ነኝ። ሁሉም እውነተኛ አማኞች ከእርሱ ጋር ይሰለፋሉ።** በእግዚአብሔር በተመለሰችው ሙሽራ-ቤተ ክርስቲያን በኩል እንደሚከሰቱ ቃል የገባቸውን ታላላቅ ነገሮች በቅርቡ መጠበቅ እንችላለን። ሁላችንም በክርስቶስ አካል ውስጥ ቦታችንን ማግኘት አለብን ጌታ ከራሱ ጋር ያዋህደናል እናም የተመረጡትን ከሁሉም ዘመን ታላቁን ድል እንዲያገኙ ይመራቸዋል። እነርሱ ተስፋዎች የተሰጧቸው አሸናፊዎች ይሆናሉ። ከጽሑፍ ቃሉ ጋር ስንተባበር፣ ሁሉን ቻይ ከሆነው እግዝአብሔር የመጨረሻውን መጀመር መጠበቅ እንችላለን። የእግዚአብሔር ኃይል የሚገለጽበት "ሕያው የተነገረ ቃል" ይሆናል

እንደተስፋውም አምላክ ምድርንና ሰማያትን አንድ ጊዜ ደግሞ ያናውጣል (ዕብ.12፡26) በዚያ ጊዜ የሚከተለው ቅዱስ ጽሑፍ ይፈጸማል፣ "እኔ እሰማለሁ ይላል እግዚአብሔር፣ እኔ ሰማያትን እሰማለሁ፣ እነርሱም ምድርን ይሰማሉ" (ሆሴ.2፡21)። አማኞችም ድርሻ ይኖራቸዋል፣ በዘካ.10፡1 ላይ እንደተጻፈው፣ "በመጨረሻው ዝናብ ወራት ዝናብን ከጌታ ዘንድ ለምኑ፤ ጌታም ደመናን ያበራል፣ የዝናብንም ደመና ይሰጣቸዋል..." ከዚህ በፊት እንደተገለጸው፣ ይህ ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት የሚመጣው የመጽናናት ጊዜ ይሆናል። በእውነትም የአዝመራ ጊዜ ነው! የአዝመራው ጌታ እንደነገረን፣ "በዚያን ጊዜም ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፡- መከሩ ብዙ ነው፣ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው። ስለዚህም የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑ" (ማቴ.9፡37-38)።

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣

ስምህ ይቀደስ።

መንግሥትህ ትምጣ።

ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን።

የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን።

እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣

በደላችንን ይቅር በለን። ከክፉ አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን።

መንግሥት ያንተ ናትና፣

ኃይልና ክብርም ለዘላለም የአንተ ነውና። አሜን።

**“ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት እና ዛሬ እስከ ዘላለም ያው ነው” (ዕብ.13፡8)**